ማስታወሻ: በቀይ የተሰጡ አስተያየቶች በምክር ቤቱ አባል በሰይፈልዴይን (Seifeldein) የቀረቡ ሲሆን በከተማው ምክር ቤትም ግምት ውስጥ ይገባል

ደንብ ቁጥር _______

የአሌክሳንድሪያ ከተማ ምክር ቤት፣ ቨርጂኒያ በ1981 ያወጣውን ደንብ ርዕስ ቁጥር 2 (“አጠቃላይ መንግስት”) ምዕራፍ 4 (“ኮሚቴዎች፣ ቦርዶች እና ኮሚሽኖች”) በተሻሻለው መሰረት አዲስ አንቀጽ AA (“የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ቦርድ”) በማከል ለማሻሻል የወጣ ደንብ።

የአሌክሳንደሪያ ከተማ ምክር ቤት የሚከተለውን ደንግጓል፡

ክፍል 504። የአሌክሳንደሪያ ከተማ ምክር ቤት፣ ቨርጂኒያ፣ 1981 ያወጣው ደንብ ርዕስ ቁጥር 2 ምዕራፍ 4 አዲስ አንቀጽ AA, “ገለልተኛ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ቦርድ” በማከል በሚከተለው መልኩ ማሻሻያ ተደርጎበታል፡

አንቀጽ AA – የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ቦርድ

**ክፍል 2-4-220 የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ቦርድ**

(a) ገለልተኛ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ቦርድ (“ቦርድ”) ተብሎ የሚጠራ ኮሚሽን በዚህ ደንብ መሰረት ተቋቁሟል። በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመው ቦርድ የስራ እንቅስቃሴ ከቨርጂኒያ ሕግና ደንቦች ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

**ክፍል 2-4-221 የቦርዱ ዓላማ እና ወሰን**

(a) ዓላማ፡ የቦርዱ ዓላማ የፖሊስን ቅቡልነት ማጎልበትና በፖሊስ መምሪያ፣ በከተማ ምክር ቤት፣ በከተማ ስራ አስኪያጅና በሕዝቡ መካከል ያለውን መተማመን ለማሳደግ ነው። ቦርዱ፡ በአሌክሳንደሪያ ውስጥ የሚሰጡትን የፖሊስ አገልግሎቶች፣ አሰራሮች፣ የአሰራር ስርዓቶችና ውጤቶችን በተመለከተ ወቅቱን የጠበቀ፣ ፍትሐዊና ምክንያታዊ ግምገማ፣ ምርመራና ምዘና ያደርጋል፤ በራሱ ያገኛቸውን በዘርና በማህበራዊ መሰረት ላይ የተፈጠሩ የእኩልነት እጦትን ጨምሮ አድሎአዊ አሰራሮችን ለማስተካከል የታለሙ ትርጉም ያላቸው ምዘናዎችን በማድረግ የእርምት ምክረ ሃሳቦችን ይሰጣል፤ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ስርዓትን ጨምሮ በሚመከሩ እርምጃዎችና ማሻሻያ አማካይነት ሁሉም ማህበረሰቦች ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤ እነዚህን ማሻሻያዎችም በማህበረሰባችን ውስጥ በሚገባ ለመተግበር የሚያስችሉ ስልቶችን ይጠቁማል።

(b) ወሰን፡ ቦርዱ በክፍል 2-4-227 ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች ይመረምራል፣ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የአሌክሳንደሪያ ፖሊስ መምሪያ (APD) ያካሄዳቸውን ምርመራዎች ይገመግማል፣ በአሌክሳንደሪያ ውስጥ ያሉ የፖሊስ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎች፣ የአሰራር ስርዓቶችና ውጤቶችን ይመዝናል፣ የደረሰባቸውን ግኝቶች ይፋ ያደርጋል፣ አሌክሳንድሪያ ውስጥ አግባብነት ያለው ዲስፕሊን፣ የፖሊስ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርዓቶች እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚችሉ ምክረ ሃሳቦችንም

ማስታወሻ: በቀይ የተሰጡ አስተያየቶች በምክር ቤቱ አባል በሰይፈልዴይን (Seifeldein) የቀረቡ ሲሆን በከተማው ምክር ቤትም ግምት ውስጥ ይገባል

ለከተማው ምክር ቤት፣ ለከተማው ስራ አስኪያጅ፣ ለት/ቤት ቦርድ፣ ለት/ቤት ዋና ተቆጣጣሪ፣ ለ APD እና ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች ያቀርባል። ቦርዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያከናውን ተፈቅዶለታል፡

(c) የተቀመጠለትን የስልጣን ወሰንና የተፈቀዱለትን ተግባራት እንዲያከናውንና በስልጣን ወሰኑ ውስጥ የተደነገጉትን ሒደቶችና ደንቦች ይበልጥ ዘርዘር አድርጎ ለማስቀመጥ፣ወይም ቦርዱ ከ APD ጋር የመግባቢያ ሰነድ(“MOU”) ይፈራረማል። የመግባቢያ ሰነዱን መፈራረም ያለባቸው የፖሊስ አዛዥና የከተማው ስራ አስኪያጅ ናቸው። ወይም ወይ የቀደመውን ዓረፍተ-ነገር ይሰርዙ ወይም ያክሉ “እንደዚህ ያሉ ፊርማዎች ያለ አግባብ እንዳይታገዱ።” (የሰይፈልዴይን (Seifeldein) አስተያየት)የመግባቢያ ሰነዱ በቦርዱና በ APD መካከል የሚኖሩ ግንኙነቶችና የጋራ ግዴታዎችን በግልጽ የሚያስቀምጥ መሆን አለበት። ቦርዱ በከተማው ምክር ቤት በሚሾምለት ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ እና በከተማው አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት እየታገዘ የዚህ የመግባቢያ ሰነድ ድንጋጌዎች ላይ እንዲደራደር ተፈቅዶለታል ወይም የከተማውን የአቃቤ ህግ ቢሮ ወደ ወደ ህግ ጠበቆች መቀየር።” የመግባቢያ ሰነዱ ድንጋጌ ከዚህ የማቋቋሚ ደንብ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ከሆነ፣ የደንቡ ድንጋጌ የጸና ይሆናል።

(d) ቦርዱ የተሰጠውን የስልጣን ወሰን ለማስፈጸምና የተፈቀዱለትን ተግባራት ለማከናወን አስፈላጊ ናቸው ብሎ እንዲቀርቡለት የሚጠይቃቸውን በ APD ወይም በከተማው ይዞታ ስር የሚገኙ ሁሉም መዛግብት፣ ሰነዶችና ማቴሪያሎች ይዞታቸው ሳይቀየር ሊቀርቡ ይገባል። እነዚህ ሰነዶች በቨርጂኒያ የመረጃ ነጻነት አዋጅ መሰረት ሚስጥራዊ ሆኖ መቆየት ያለበትን ሚስጥራዊ መረጃ ከያዙ፣ ሚስጥራዊነትን ለማስጠበቅ ሲባል ቦርዱ እነዚህን ሰነዶች የሚመለከተው በዝግ ስብሰባ ነው። የተጠየቁት ሰነዶች አሁን በመካሄድ ላይ ያለ የወንጀል ምርመራ መዝገብ አካል ከሆኑና ሒደቱ፣ ማስረጃው፣ ዘዴዎቹ፣ ወሰኑ ወይም በምርመራው ውስጥ ያሉ ሌሎች ጉዳዮች መገለጻቸው የምርመራውን ሒደት ለአደጋ የሚያጋልጠው ከሆነ፣ APD ምርመራውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ ወይም የወንጀል ምርመራው ከዚህ በኋላ ለአደጋ እንደማይጋለጥ እስከሚወሰን ድረስ እነዚህን ሰነዶች ለማቅረብ አይገደድም።

የሰይፈልዴይን (Seifeldein) አስተያየት፣ APD ተመሳሳይ ምርመራዎችን ለመፍቀድ የወንጀል ምርመራ ጊዜ ምንም ይሁን ምን ሰነዶችን እንዲያቀርብ መጠየቅ ። ሆኖም ሰነዶቹ የግል ሆነው የሚቆዩ እና የወንጀል ምርመራዎች እስኪያጠናቅቁ ድረስ በይፋ አይገለጽም ።

(e) ቦርዱ ከገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ በሚደረግለት እገዛ መሰረት ከነባር የፌዴራልና የግዛት ሕግ፣ ከግዛት ደንብና ከዚህ ማቋቋሚያ ደንብ ጋር በተጣጣመ መልኩ የራሱን የመተዳደሪያ ደንብ፣ አስተዳደራዊ ስርዓትና የአሰራር ፖሊሲዎችና ስርዓቶችን ማዘጋጀት ይችላል። እንዲህ ዓይነት የመተዳደሪያ ደንቦች በቦርዱ ከመጽደቃቸው በፊት ለሕዝብ ይፋ መደረግና በሕዝባዊ ውይይት መዳበር አለባቸው፣ ተግባራዊ የሚሆኑትም በከተማው ምክር ቤት ሲፀድቁ ነው።

ማስታወሻ: በቀይ የተሰጡ አስተያየቶች በምክር ቤቱ አባል በሰይፈልዴይን (Seifeldein) የቀረቡ ሲሆን በከተማው ምክር ቤትም ግምት ውስጥ ይገባል

(f) ቦርዱ ተግባሩን ለማከናወን ይችል ዘንድ ለቦርዱና ለገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ቢሮ ከከተማው ምክር ቤት አመታዊ በጀትና የመጠባበቂያ ገንዘብ ይመደብላቸዋል፤ ይህን ገንዘብም ጥቅም ላይ መዋል ያለበት በሚከተሉት መሰረት ነው፤

i. የቦርዱና የገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ቢሮ ዓላማዎችና የስልጣን ወሰን መሰረት፤
ii. MOU ከ APD እዝህ ጋር ያስፈልጋል ወይም ii ይሰረዝ (የሰይፈልድን (Seifeldein) አስተያየት)
iii. የከተማው ምክር ቤት በሚያፀድቀው በጀትና የመጠባበቂያ ገንዘብ መሰረትና
iv. በከተማው የግዥና የውጭ አስተዳደር ደንቦችና አሰራሮች መሰረት ነው።

(g) (ሰ) ቦርዱ በገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ በኩል ከቦርዱ ምርመራ ወይም ለቦርዱ ወይም ለ APD ከቀረቡ ቅሬታዎች ግምገማ ጋር የተያያዙ ሁሉንም የ APD ሪፖርቶች፣ ፋይሎችና መዛግብት ያለገደብ ማግኘት ይችላል።

**ክፍል 2-4-222 የቦርድ አባላት መስፈርትና የአገልግሎት ዘመን**

(a) ቦርዱ በከተማው ምክር ቤት የሚሾሙ ሰባት ድምፅ የሚሰጡ አባላት ይኖሩታል፣ ምክር ቤቱም የከተማውን ብዝሃነት የሚያንጸባርቅ ፍትሐዊ፣ ምክንያታዊ፣ ገለልተኛ፣ ብዝሃነት ያለበትና ወካይ የሆነ አካል ለመፍጠር ጥረት ማድረግ አለበት።

(b) ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው ሰባቱ የቦርዱ አባላት የአሌክሳንድሪያ ከተማ ነዋሪዎች መሆን አለባቸው፣ ፍትሃዊነት ቅንነትና ምክንያታዊነት የተላበሱ መሆንም አለባቸው፤ ወይም "በምክር ቤቱ ምርጫ (የሰይፈልድን (Seifeldein) አስተያየት)" የከተማው ምክር ቤት የሚመርጣቸው ድምፅ የሚሰጡ የቦርድ አባላት ከሚከተሉት ቡድኖች የተወከሉ መሆን አለባቸው (አንድ አባል ከአንድ በላይ ቡድን መወከል ይችላል)፡ ወይም "በቦርዱ ግዴታዎች አፈፃፀም ጋር በተዛመደ በሙያ እና በልምድ መሠረት ይመረጣል" የሚለው ይሰረዝ።" (የሰይፈልድን (Seifeldein) አስተያየት) የከተማው ምክር ቤት የሚመርጣቸው ድምፅ የሚሰጡ የቦርድ አባላት ከሚከተሉት ቡድኖች የተወከሉ መሆን አለባቸው (አንድ አባል ከአንድ በላይ ቡድን መወከል ይችላል)፡

i. ቢያንስ ሶስቱ አባላት በታሪክ፣ በዘር ወይም በማህበራዊ ምክንያት ከሌላው የተገለሉና በአሌክሳንድሪያ ወይም በቨርጂኒያ የጋራ ብልጽግና ግዛት ውስጥ ተገቢ ያልሆነ የፖሊስ እንግልት ከሚደርስባቸው ማህበረሰቦች የመጡ መሆን አለባቸው፤
ii. የዘር ወይም ማህበራዊ ፍትሕን የሚጠይቅ ወይም በታሪክ፣ በዘር ወይም በማህበራዊ ምክንያት ከሌላው ማህበረሰብ ለተገለሉ ማህበረሰቦች፣ በተለይም የፖሊስ እንግልት ለደረሰባቸው ማህበረሰቦች መብት የሚሟገት ድርጅት፣ ቢሮ ወይም ኤጀንሲን የሚወክል ቢያንስ አንድ አባል፤ እና
iii. በሕግ ማስከበር ሙያ ልምድ ያለው፣ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በሕግ ማስከበር ስራ ላይ ያልተሰማራ ወይም የቅርብ የቤተሰብ አባሉ በአሁኑ ጊዜ በሕግ ማስከበር ስራ ላይ ያልተሰማራ ድምፅ የማይሰጥና በሙያዊ ብቃቱ የሚመረጥ ቢያንስ አንድ አባል። "ወይም

በተቀጠረ 5 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከህግ አስከባሪ ተወግደዋል" ን ይጨምሩ (የሰይፈልዲን (Seifeldein) አስተያየት)

(c) ድምፅ የሚሰጥ አባል በአሁኑ ጊዜ የከተማው አስተዳደር ተቀጣሪ፣ ለመንግስት ቢሮ እጩ ተወዳዳሪ፣ ተመራጭ ባለስልጣን፣ የቀድሞ የ APD ሰራተኛ፣ በአሁኑ ጊዜ ወይም በቀድሞ ጊዜ የ APD ሰራተኛ የሆኑ የቅርብ ቤተሰብ አባል ያለው፣ በአሁኑ ጊዜ የ APD ሰራተኛ ወይም በአሁኑ ጊዜ የሕግ አስከባሪ ኤጄንሲ ሰራተኛ መሆን የለበትም።

(d) ጊዜያዊ አባላትን ከሚተኩት የቦርድ አባላት በስተቀር፣ አባላት የሚመረጡት ለሶስት ዓመት ሲሆን ይህ የአገልግሎት ዘመን የሚያበቃበት ቀንም ሜይ 31 ይሆናል። የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ሳይጠናቀቅ የተወሰኑ አዳዲስ አባላት የሚመረጡበትን ስርዓት ይከተላል። ለዚህም ሲባል፣ የከተማው ምክር ቤት የመጀመሪያውን ቦርድ ሶስት ድምፅ የሚሰጡ አባላት ለ18 ወራት የሚሾም ሲሆን አራት ድምፅ የሚሰጡ አባላት ደግሞ ለሶስት ዓመት ይሾማሉ። አንድ የቦርድ አባል በየሶስት ዓመቱ ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ሊመረጥ ይችላል።

(e) የቦርዱ የአሰራር ስርዓቶች በዚህ ምዕራፍ ካልተሻሻለ በስተቀር የከተማውን ደንብ ክፍል 2-4-1 እና ተከታዮቹን መሰረት ማድረግ አለባቸው።

**ክፍል 2-4-223 የጥቅም ግጭቶች እና ሚስጥራዊነት**

(a) ቦርዱ እና እያንዳንዱ አባል በቨርጂኒያ ደንብ ቁጥር §§ 2.2-3100 እና ተከታዮቹ ስር ያለውን የቨርጂኒያ ግዛት እና የአካባቢ መንግስት የጥቅም ግጭቶች ሕግ ማክበር አለባቸው።

(b) በቨርጂኒያ የመረጃ ነጻነት ሕግ እስከሚፈቅደው ድረስ፣ እያንዳንዱ አባል ሁሉንም ሚስጥራዊ ወይም ለተወሰነ ሰው ብቻ የሚታዩ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅ አለበት፣ እነርሱም የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡

i. አባሉ በቦርዱ ውስጥ በሚያገለግልበት ወቅት የሚቀርቡለት የዲስፕሊን እርምጃዎች፣ ማስታወሻዎችና ሪፖርቶች።
ii. መግለጫ እንዲሰጥ በ APD የተጠየቀ የፖሊስ መኮንን ወይም የ APD ሰራተኛ መግለጫዎች።
iii. የወንጀል ምርመራ መዝገቦች።

ወይም ክፍል ለ ን ይሰርዙ (የሰይልፈድን Seifeldein አስተያየት)

**ክፍል 2-4-224 ምልዓተ ጉባኤ፣ ድምፅ አሰጣጥ እና ስብሰባዎች**

(a) በዚህ አንቀጽ ማሻሻያ ካልተደረገበት በስተቀር፣ ቦርዱ የቦርድ እና የኮሚሽኖች የአሰራር ስርዓቶችን ድንጋጌ አንቀጽ ኤ ወይም ርዕስ 2፣ ምዕራፍ 4 ማክበር አለበት።

ማስታወሻ: በቀይ የተሰጡ አስተያየቶች በምክር ቤቱ አባል በሰይፈልዴይን (Seifeldein) የቀረቡ ሲሆን በከተማው ምክር ቤትም ግምት ውስጥ ይገባል

(b) ቦርዱ ስራውን ለማከናወን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ስብሰባ የሚያደርግ ቢሆንም፣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ግን ከአራት ጊዜ በታች ስብሰባ ማድረግ የለበትም።

(c) የቦርዱ ስብሰባዎች በሁሉም መስክ የቨርጂኒያ የመረጃ ነጻነት ሕግን የስበሰባ ድንጋጌዎች ማሟላት አለባቸው፤ ርዕሰ ጉዳዩ በዝግ ስብሰባ እንዲታይ በሕግ የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ስብሰባውን ለሕዝብ ክፍት ማድረግ በዚህ ውስጥ ይካተታል።

(d) ቦርዱ ማንኛውንም ውሳኔ ለማሳለፍ ከሰባቱ ድምፅ ሰጪ አባላት ቢያንስ አምስቱ ወይም አራቱ(የሰይልፈድን Seifeldein አስተያየት) መገኘት አለባቸው።

(e) ቦርዱ የስብሰባዎቹን ቃለ ጉባኤ መያዝ ያለበት ሲሆን ቃለ ጉባኤውም የሚከተሉትን መረጃዎች ያካትታል፡

i. እያንዳንዱ ስብሰባ የተደረገበት ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፤
ii. በስብሰባው ላይ የተገኙና ያልተገኙ አባላት፤
iii. ለስብሰባ የቀረበ አጀንዳ፣ የተደረገ ውይይት ወይም የተወሰነ ውሳኔ፤ እና
iv. የተሰጡ ድምፆች ብዛት መዝገብ።

(f) የቦርዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች የሕዝብ ንብረቶች ናቸው፣ በቨርጂኒያ የመረጃ ነጻነት ሕግ መሰረት ምርመራ ይደረግባቸዋል።

**ክፍል 2-4-225 ለቦርዱ የሚደረግ ድጋፍ**

(a) የቦርድ ሰራተኞች

i. የከተማው ምክር ቤት በዚህ ደንብ ክፍል 4-1-5 እና 4-1-6 መሰረት ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ የሚሾም ሲሆን የመርማሪው ተግባር ደግሞ ለቦርዱ ሰራተኞችን መመደብና የቦርዱን አስተዳደራዊ ተግባራት ማስተባበር ነው።
ii. ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪው ለቦርዱ የተሰጡትን የምርመራ ስራዎች ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ መርማሪዎችን ይቀጥራል። እነዚህም መርማሪዎች በምርመራ ስራው ፍላጎት መሰረት የትርፍ ጊዜ አማካሪዎች ወይም የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ።
iii. የከተማው ዋና አቃቤ ሕግ ወይም ተወካዩ የቦርዱ የሕግ አማካሪ ሆኖ ያገለግላል። አንድ የተለየ ጉዳይን በተመለከተና የከተማው አቃቤ ሕግ ቢሮ ውጤታማ በሆነ መንገድ የሕግ ውክልና ስራውን እንዳይፈጽም የሚያደርግ የጥቅም ግጭት ሲኖር፣ የከተማው አስተዳደር ቦርዱን የሚያማክር ጠበቃ ከሌላ ቦታ መቅጠር አለበት። ወይም የቀደመውን ሰርዝ እና አክል “ቦርዱ እና ቦርዱ ፊት ለፊት በሚቀርቡ የሕግ ጉዳዮች ላይ ቦርዱን እና የፖሊስ ኦዲተር / መርማሪን ለማማከር ቦርዱ ከውጭ የሕግ አማካሪ ይቀጥራል ።” ወይም “በቦርዱ ፊት ለፊት በሚቀርቡ የሕግ ጉዳዮች ላይ ለቦርዱ እና ለፖሊስ ኦዲተር / መርማሪ ምክር ለመስጠት እንደ አስፈላጊነቱ ከህግ አማካሪነት የሚለው ይቆይ ። የከተማው ጠበቃ

ወይም ተወካዩ በቦርዱ ውጭ አማካሪ በማይፈልግበት ወይም የግጭት ስጋት በማይኖርበት ሁኔታ የቦርዱ የሕግ አማካሪ ሆነው ያገለግላሉ "(የሰይልፈድን Seifeldein አስተያየት)

(b) ከከተማው አስተዳደር የሚደረግ ሌላ ድጋፍ

i. በከተማ አስተዳደሩ ድህረ ገጽ ላይ የሚስተናገድ ድህረ ገጽ ለቦርዱ መከፈት አለበት። አግባብነት ባላቸው የፌዴራል፣ የግዛት እና የአካባቢ ሕጎች እስከተፈቀደ ድረስም በቦርዱ ድህረ ገጽ ላይ የሚለጠፉ ነገሮችን የሚቆጣጠረው ቦርዱ ነው።

ii. ሁሉም የቦርዱ ግልጽ ስብሰባዎች በቪድዮ ተቀርጸው በከተማ አስተዳደሩ ድረ ገጽ ላይ ሕዝብ ሊያያቸው ይገባል።

iii. ከተማ አስተዳደሩ ከገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ በሚያገኘው ድጋፍ መሰረት በቦርዱ ድህረ ገጽ ላይ የሚለጠፉ ወይም የሚወገዱ ልጥፎችን በተመለከተ በቦርዱ ውሳኔ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት ወይም "ተገቢ ያልሆነ" ቃል (የሰይልፈድን Seifeldein አስተያየት) የሚለዉን ማስወገድ የለበትም።

iv. የቦርዱ አባላት የከተማ አስተዳደሩ የኢ-ሜይል አድራሻ የሚሰጣቸው ሲሆን ይህን ኢ-ሜይል አድራሻ መጠቀም የሚችሉት ከቦርዱ ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች ብቻ ነው።

v. የከተማ አስተዳደሩ፣ ሁሉም የከተማው የስራ ክፍሎች፣ ቦርዶች፣ ኮሚሽኖችና ሰራተኞች ከቦርዱ ጋር ለመተባበር በቅን ልቡና ጥረት ማድረግ አለባቸው፣ ከቦርዱ ለሚቀርቡላቸው ምክንያታዊ ጥያቄዎች መተባበር ወይም የማይተባበሩበትን ምክንያት በፍጥነት ማሳወቅ አለባቸው።

## ክፍል 2-4-226 የቦርድ ስልጠና

የቦርድ አባላት በሁለት ዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜና ለቦርድ አባልነት በተመረጡ በስድስት ወራት ውስጥ በሚከተሉት ስልጠናዎች ላይ መሳተፍ አለባቸው፡

(a) የሕግ ማስከበር የወንጀል ተቆጣጣሪ ብሄራዊ ማህበር ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ያለው ድርጅት የሚሰጠው ቢያንስ ስምንት ሰዓት የሚፈጅ ስልጠና።

(b) በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በማተኮር የሚመለከታቸው የከተማ አስተዳደሩ ሰራተኞች የሚሰጡት ስልጠና፡

i. የሕዝባዊ ቦርድ አባላት ሕጋዊና ስነ ምግባራዊ ግዴታዎች፤

ii. የ APD ፖሊሲዎችና ስልጠና፣ መከላከል ላይ የተመሰረተ የታክቲክ ስልጠና፣ በቀውስ ወቅት ጣልቃ የመግባት ስልጠና እና ነገሮችን የማርገብ ስልጠናን ጨምሮ፤

iii. ከፖሊስ ስራዎች ጋር በተያያዘ ተጠያቂነት፣ የሰራተኛ ዲስፕሊንና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው የግላዊነት ደንቦችና የከተማ ፖሊሲዎችና አሰራሮች፤ እና

iv. APD እና የከተማ አስተዳደራዊ ስርዓቶች፣ ሒደቶች፣ መዋቅሮችና ስራዎች።

(c) በዓመት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ከ APD የፓትሮል ስራዎች ጋር አብረው በመጓዝ የሚደረጉ ክፍለ ጊዜያት።

(d) የከተማ አስተዳደሩና ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ለቦርድ አባላት ተጨማሪ ስልጠና ይሰጣሉ፤ ይህም በአእምሮ ጤና፣ የስሜት ቀውስን ያገናዘበ የፖሊስ አገልግሎት፣ የሲቪል መብቶችና የሕገ መንግስት ሕግ፣ ዘርና ስርዓታዊ ዘረኝነት፣ የማህበረሰብ አደረጃጀትና አውትሪች፣ ግልግል፣ ምርመራ፣ የፖሊስ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎችና አስተዳደርን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የዘርፉን ኤክስፐርቶች በማቅረብ የሚሰጡ ተዘማጅ ስልጠናዎችን ይጨምራል።

## **ክፍል 2-4-227 የቦርዱ ግዴታዎች**

(a) የቦርድ ዝግጁነት የውሳኔ ሃሳብ

i. የመጀመሪያዎቹ የቦርድ አባላት በከተማው ምክር ቤት ከተሾሙ በኋላ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ፣ ቦርዱ አሰራሮቹንና የአሰራር ስርዓቶቹን ለመዘርጋት ስብሰባ ማድረግ አለበት። ቦርዱ ቅሬታዎችን እንዴት እንደሚቀበል፣ የምርመራ ስራዎች እንዴት እንደሚካሄዱ የአሰራር ስርዓቶቹን ካስቀመጠና በክፍል 2-4-221(c) መሰረት መፈረም ያለበት የመግባቢያ ሰነድ በሁለቱም ወገኖች ከተፈረመ፣ ቦርዱም በቂ ሰራተኛ ከተመደበለት፣ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሰረት የተጣሉበትን ኃላፊነቶች ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን የሚያመለክት የውሳኔ ሃሳብ ማሳለፍ አለበት። ቦርዱ ይህን የውሳኔ ሃሳብ እስከሚያሳልፍ ድረስ በአሁኑ ጊዜ እየታየ ያለ ቅሬታ የመቀበል ወይም ቅሬታዎችን የመመርመር ሒደት ለቦርዱ መተላለፍ አይችልም።

(b) ቅሬታ መቀበል

i. ቦርዱ የ APD የሕግ አስከባሪ መኮንኖችና ሲቪል ሰራተኞችን ስነ ምግባር በተመለከተ ከማህበረሰቡ የሚቀርቡ ቅሬታዎችንየመቀበያና እንደ ቅሬታው ዓይነትም ቅሬታዎችን ወደ APD ወይም ወደ ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ለምርመራ የመላኪያ ሒደት አዘጋጅቶ ያስተዳድራል። ይህ ሒደት በቨርጂኒያ ሕግ § 9.1-600 ላይ እንደተገለጸው APD የማህበረሰብ ቅሬታዎችን ለመቀበል በአሁኑ ጊዜ ከሚከተላቸው ማናቸውም ነባር የአሰራር ስርዓቶች የተለየና ራሱን የቻለ ነው፤

ii. ለቦርዱ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ቦርዱ የሚያዘጋጀውን ቅጽ በመጠቀም ማቅረብ ይቻላል ወይም ቅሬታ አቅራቢው በቃል ማቅረብ ይችላል። በቃል የሚቀርቡ ቅሬታዎች ቦርዱ በሚያዘጋጀው የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ የሰፈረውን መረጃ መያዝ አለባቸው።

iii. ቅሬታ ለቦርዱ የሚቀርብበትን ሒደት የሚመለከት መረጃ፣ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾችና ቦርዱንና የስልጣን ወሰኑንና ዓላማውን የሚመለከቱ አጠቃላይ መረጃዎች በኦንላይን እና በገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ቢሮ፣ በ APD፣ በሰብአዊ መብቶች ቢሮ እንደዚሁም እነዚህን ቅጾችና

መረጃ በስፋት ተደራሽ ለማድረግ ውጤታማ ተደርገው በሚቆጠሩ ሌሎች ቦታዎችም ዝግጁ ይደረጋሉ።

iv. ቅሬታ ለቦርዱ የሚቀርብበትን ሒደት የሚመለከት መረጃ፣ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾችና ቦርዱንና የስልጣን ወሰኑንና ዓላማውን የሚመለከቱ አጠቃላይ መረጃዎች በእንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ እና አረብኛ እንደዚሁም ቅሬታውን ለቦርዱ የሚያቀርበው ሰው በሚጠይቀው ሌላ ተጨማሪ ቋንቋ ዝግጁ ይደረጋሉ።

v. የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች ክስተቱን የተመለከቱ መረጃዎችን የሚጠይቁ ሲሆን፣ እነርሱም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

1) የቅሬታ አቅራቢው ሰው ስም፣ አድራሻና የመገኛ አድራሻ፤
2) የቅሬታውን ምክንያት የሚያስረዳ መግለጫ፤
3) አሳሳቢ የሆነው የፖሊስ ባህሪ መግለጫ፤
4) ባህሪው የታየበት ክስተት መግለጫ፤ እና
5) ክስተቱ ሲፈጸም ያዩ ወይም የሚያውቁ የቅሬታ አቅራቢው ምስክሮችን የሚመለከት መረጃ፤ ቅሬታው በቀረበበት ወቅት የሚታወቅ ከሆነም ስማቸው፣ አድራሻቸውና የስልክ ቁጥራቸው።

ቅሬታ አቅራቢው ሁሉንም መረጃ በቅጹ ላይ አለመሙላቱ ብቻ ቅሬታውን ከመታየት አያግደውም። ወይም "በቅጹ ላይ ያለውን መረጃ በሙሉ አለማቅረብ ምርመራው እንዳይካሄድ አያግደውም የሚለውን ጨምር።" (የሰይልፈድን Seifeldein አስተያየት)

vi. በዚህ ውስጥ በንኡስ ክፍል (መ) ውስጥ ከተለዩት ጉዳዮች በስተቀር፣ APD ለ APD ወይም ለቦርዱ የቀረቡ ቅሬታዎችን መመርመሩን መቀጠል አለበት። AP የቅሬታውን ምርመራ ለማጠናቀቅ ወይም "በቦርዱ ግምገማ ውስጥ ያልነበሩትን" በመጨመር "የጥሩ እምነት ጥረትን" (የሰይፈልዲን አስተያየት) ይሰረዝ እንዲሁም) በስልሳ (60) ቀናት ውስጥ ለቦርድ የምርመራ ሪፖርት ያቀርባል ። ቦርዱ ((የሰይልፈድን Seifeldein አስተያየት))በመካሄድ ላይ ያለ የወንጀል ወይም አስተዳደራዊ ምርመራን ለመከላከል ከፖሊስ አዛዡ ጥያቄ ሲቀርብለት፣ በሰራተኛ የቀረበ ቅሬታ በከተማ አስተዳደራዊ ደንብ 6-21፣ በሕግ አስከባሪ መኮንኖች የአሰራር ስርዓት ዋስትና ሕግ (በቨርጂኒያ ሕግ ርዕስ 9.1 ስር የተጠቃለለ) ) ወይም በፍርድ ቤት እየታየ ከሆነ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ) የ 60 ቀን ጊዜውን ሊያራዝም "ይችላል"፣ ይህንኑም ለቅሬታ አቅራቢውና ለከተማው ምክር ቤት ያሳውቃል። ወይም "ለመልካም ነገር" ከተጨመረ በኋላ ሁሉንም ነገር ይሰርዙ (የሰይልፈድን Seifeldein አስተያየት)

vii. ይህ ሒደት በቨርጂኒያ ሕግ § 9.1-600; ላይ እንደተገለጸው APD የማህበረሰብ ቅሬታዎችን ለመቀበል በአሁኑ ጊዜ ከሚከተላቸው ማናቸውም ነባር የአሰራር ስርዓቶች የተለየና ራሱን የቻለ ነው፤

(c) የ APD ምርመራዎችን ቦርዱ ዳግም የሚያይበት ሁኔታ

i. ከዚህ በታች (መ) ስር ከተዘረዘሩት ቦርዱ ምርመራ ከሚያካሂድባቸው ጉዳዮች በስተቀር፣ ቦርዱ የ APD የውጭ ጉዳይና ሙያዊ ሃላፊነት ቢሮ (OEAPR) የ APD የሕግ አስከባሪ መኮንኖችና ሲቪል ሰራተኞችን ስነ ምግባር በተመለከተ የሚያካሂዳቸውን ምርመራዎች ሁሉ ድጋሚ ሊመረምር ይችላል፤ ይህም ለ APD ወይም ለቦርዱ የቀረበ ቢሆንም ባይሆንም የምርመራውን ጥልቀት፣ ምሉእነት፣ ትክክለኛነት፣ ምክንያታዊነትና ከአድሎ ነጻ መሆኑን እንደዚሁም በዚህ የምርመራ ውጤት ምክንያት የተወሰደው የዲስፕሊን እርምጃ በቂ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ቦርዱ ራሱ በሚያወጣውና በጽሑፍ በሚያስቀምጠው መስፈርት መሰረት የዳግም ምርመራ ስራውን በተመረጡ የምርመራ ጉዳዮች ወይም የተወሰነ ባህርይ ባላቸው ምርመራዎች ላይ በማተኮር ብዛቱን ሊቀንስ ይችላል።

ii. ቦርዱ የሕዝባዊ ውይይትን ጨምሮ የምርመራ ስራ ግምገማን ካጠናቀቀ በኋላ ከሚከተሉት ግኝቶች አንዱ ላይ ሊደርስ ይችላል፡

1) በምርመራ ሪፖርት ውስጥ በዝርዝር የተቀመጡት ሁሉም ግኝቶችና ውሳኔዎች ጋር በሙሉ ወይም በከፊል ሊስማማ ይችላል፤

2) ግኝቶቹ ለ APD በቀረበሉት መረጃዎች በበቂ ሁኔታ አለመደገፋቸውን ለከተማው ምክር ቤት፣ የከተማው ስራ አስኪያጅና ለ APD በማሳወቅ የፖሊስ አዛዡ ጉዳዩን በድጋሚ እንዲያዩት ምክረ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል፤ ወይም

3) በቦርዱ እይታ መሰረት ምርመራው ያልተሟላ መሆኑን ለከተማው ምክር ቤት፣ ለከተማው ስራ አስኪያጅና ለ APD በማሳወቅ ተጨማሪ ምርመራ እንዲካሄድ ምክረ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል።

ወይም ይጨምሩ

4) ምክር ቤቱን ፣ የከተማ አስተዳዳሪውን ፣ APD, እና ማህበረሰቡን በቦርዱ ውሳኔ እምነት ከማስረጃው በተቃራኒው የተሳሳቱ እንደሆኑ ይመክራሉ ። (የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት)

የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት ለቦርዱ እርምጃ ተጨማሪ አማራጮችን ያክሉ ።

(መ) ቦርዱ በቅሬታዎችና ክስተቶች ላይ የሚያካሂደው ምርመራ

i. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ክስተቶች በቅሬታ መልክ የቀረቡ ቢሆኑም ባይሆኑም የምርመራ ስራውን የሚያካሂደው ገለልትኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ሲሆን፣ ይህን የሚያካሂደውም ቦርዱን በመወከል ነው፡

1) “ሞትን የሚያስከትሉ ክስተቶች” በክስተቱ ውስጥ ተሳታፊ የነበረን ሰው ለሞት የዳረገ ማንኛውንም ክስተት ጨምሮ።

2) “ሐይል የመጠቀም” ክስተቶች፣ (i) ከፍተኛ የሆነ የሞት ስጋትን ለመፍጠር፣ (ii) ወይም “ከባድና” “ለረዥም ጊዜ የሚቆይ” የገጽታ መበላሸትም ለማስከተልኝ(የሰይፈልድን አስተያየት) ወይም (iii) የየትኛውም የሰውነት አካል ወይም እጅና እግር ከእንቅስቃሴ ውጭ እንዲሆን የሚያደርግ ሐይል መጠቀም የሚል ፍቺ ይሰጠዋል። የፖሊስ መኮንኑ ጥቃት አድራሽ መሳሪያ፣ ቴዘር ወይም ተመሳሳይ መሳሪያ፣ ኦሌዮርሲን ካፕሲከም (ዓይን የሚያቃጥል ፈሳሽ) ስፕሬይ ወይም ሌሎች ሰውነትን የሚያስቆጡ ኬሚካሎች፣ የመግደል አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ መሳሪያዎች ወይም የጦር መሳሪያ ከተጠቀመና እጆቹን ወይም ሌላ የትኛውንም የሰውነት ክፍሉን በመጠቀም የተሳተፋበትን ክስተቶች ይጨምራል።

3) “ከባድ የስነ-ምግባር ጥሰት” ማለት መደበኛ ግዴታን አለመወጣት ወይም ሕገ-ወጥ ወይም ተገቢነት የጎደለው ባህርይ ሲሆን በ AR 6-20 ውስጥ የተዘረዘሩትን የሚከተሉትን ጥፋቶችም ያካትታል፤ ይህም ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡
   a. የከተማ አስተዳደሩን መረጃዎች፣ የከተማውን ንብረት፣ መሳሪያዎች ወይም ዕቃዎች ወይም የሌላ ሰራተኛን ንብረት ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት መጉዳት፣ ማበላሸት ወይም ማውደም።
   b. የከተማ አስተዳደሩን መረጃዎች ወይም የመንግስት ንብረት ወይም የሌላ የከተማ አስተዳደሩ ሰራተኛን ንብረት መስረቅ፣ ያለአግባብ መጠቀም ወይም ያለፈቃድ ማንሳት።
   c. ደንብ መተላለፉ በሕይወት ላይ ስጋት በሚያስከትልበት ሁኔታ የደህንነት ደንቦች ወይም የቨርጂኒያ የትራፊክ ደንብን መተላለፍ።
   d. የበታች ሰራተኞችን፣ የስራ ባልደረቦችን፣ የቅርብ ሃላፊዎች ወይም የሕበረተሰቡን አባላት ማስፈራራት ወይም ዛቻ መሰንዘር።
   e. የተጣለበትን ሃላፊነት ወይም ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት አለመፈጸም ወይም የከተማውን ንብረት ያአለአግባብ መጠቀም።
   f. ከስራ ሃላፊነት ጋር በተያያዘ በስራ ሰዓት ወይም ከስራ ሰዓት ውጭ የሚፈጸም የወንጀል ወይም ሌላ የስነ-ምግባር ጥሰት ወይም ሰራተኛው በተመደበበት ቦታ መስራቱን እንዲቀጥል ወይም በየትኛውም የከተማው አስተዳደር ሃላፊነት ቦታ ላይ እንዲሰራ ቢደረግ ከተማው ለሕዝቡ ወይም ለሌሎች የከተማ እሰተዳደሩ ሰራተኞች ያለበትን ግዴታ በተመለከተ ቸልተኝነት የሚያሳይ ከሆነ።
   g. በየትኛውም የከተማዋ ኦፊሰር፣ መምሪያ ወይም ኤጀንሲ ወሰነ ስልጣን ውስጥ የሚወድቅ ማንኛውም ጉዳይ፡ (ሀ) እውነታን እያወቁ በሃሰት መቀየር፣ መደበቅ ወይም መሸፋፈን እና/ወይም (ለ) እያወቁ ማንኛውንም ሐሰተኛ፣ የተጭበረበረ ወይም አሳሳች መግለጫ ወይም መረጃ መስጠት፣ እና/ወይም (ሐ) የትኛውም

ጽሑፍ ወይም ሰነድ ሐሰተኛ፣ ኣሳሳች ወይም የተጭበረበረ መግለጫ ወይም መረጃ በውስጡ መያዙን እያወቁ ማዘጋጀት ወይም መጠቀም።

h. በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም እንኳን በስራ ቦታ ላይ የወሲብ ተግባር መፈጸም።

i. በዘር፣ በቀለም፣ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ዕድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት ወይም ጾታዊ ዝንባሌን መሰረት በማድረግ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ ጥላቻን በሚያንጸባርቅ መለኩ በቃል ወይም ሌላ ባህርይ ማሳየት።

ii. ቦርዱ ምስከሮች በገዛ ፈቃዳቸው እንዲቀርቡና መዛግብት፣ ወረቀቶችና ሌሎች ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉት ማስረጃዎችን ለማቅረብ በቅን ልቡና ላይ የተመሰረተ ጥረት ካደረገ በኋላ ምስክሮች ወይም ሰነዶቹ ካልቀረቡለት፣ወይም “በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ”(የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት) ሊመራ ወይም “ሊመራ የሚችል” የሚለዉን በማጥፋት (የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት) በማሳለፍ ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ቦርዱን ወክሎ ወይም “ለ”ን በማጥፋትና “ይሆናል”ን በመጨመር(የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት) ለአሌክሳንድሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት ማመልከቻ በማስገባት ምስክሮቹ ወይም  መዝገቦች፣ ወረቀቶችና ሌሎች ማስረጃዎች ተገድደው እንዲቀርቡ የፍርድ ቤት መጥሪያ እንዲጠይቅ ትእዛዝ ይሰጣል፤ ፍ/ቤቱምየቀረበለትን በቂ ምክንያት መሰረት በማድረግ መጥሪያው እንዲጻፍ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።  የፍ/ቤት መጥሪያ የደረሰው ማንኛውም ሰው መጥሪያውን ለጻፈው ፍ/ቤት መጥሪያው እንዲሻርለት ማመልከተ ይችላል። ወይም የመጨረሻውን አረፍተነገር ይሰርዙ(የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት)

ወይም ሕጉ ከፈቀደ ያክሉ ፣ ቦርዱ ወይም መርማሪው የባሩ አባል ከሆኑ ፣ የጠበቃ ጉዳዮችን መጥሪያ መጥሪያ ማቅረብ ይችላሉ (የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት)

iii. የምርመራው ሒደት ሲጠናቀቅ፣ ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪው የምርመራ ሪፖርት የያዘውን ፋይል ለቦርዱ ያስተላልፋል። ቦርዱ በምርመራው ላይ ቢያንስ አንድ ሕዝባዊ ውይይት ማዘጋጀት አለበት። ሕዝባዊ ውይይቱ ሲጠናቀቅ፣ ቦርዱ ከሚከተሉት እርምጃዎች መካከል አንዱን ሊወስድ ይችላል፡

1) በምርመራው መዝገብና ሪፖርት መሰረተ የቀረበው ቅሬታ በማስረጃ ያልተደገፈ ነው ወይም ክስተቱ ምክንያታዊ ነበር ብሎ ከወሰነ ቅሬታውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፤

2) ቅሬታውን ወደ አሌክሳንድሪያ ከተማ የጋራ ብልጽግና አቃቤ ሕግ ሊያስተላልፈው ይችላል፤ እንዲሁም

3) የፖሊስ አዛዡ በከተማዋ የዲስፒሊን ሒደት መሰረት የዲስፒሊን እርምጃ እንዲወስዱ ምክረ ሃሳበ ሊሰጥ ይችላል።

የሰይፈልድን አስተያየት ለቦርዱ እርምጃዎች ተጨማሪ አማራቾችን ይጨምሩ

iv. APD ከቦርዱ በተሰጠው ምክረ ሃሳብ መሰረት የዲስፒሊን እርምጃ ለመውሰድ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የፖሊስ አዛዡ የቦርዱ ምክረ ሃሳብ በደረሳቸው በ30 ቀናት ውስጥ የጽሑፍ መዝገብ በማደራጀት የቦርዱን ምክረ ሃሳብ ለመተግበር ፈቃደኛ ያልሆኑበትን ምክንያት ለከተማው ምክር ቤት፣ ለከተማ ስራ አስኪያጅና ለሕዝቡ ያሳውቃሉ።

(ሠ) ቦርዱ የሚሰጣቸው የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦች

i. ቦርዱ የፖሊስን ፖሊሲ እና የአሰራር ስርዓት ዳግም ምርመራ በተመለከተ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡

1) ነባርና ለወደፊት የታሰቡ የ APD አስተዳደራዊ መመሪያዎችን መከለስና መገምገም፤ የ APD እና የሰራተኞቹ እንቅስቃሴዎች የሚመሩባቸውን ሁሉንም ደንቦች፣ ፖሊሲዎችና የአሰራር ስርዓቶች ጨምሮ፤

2) APD ከፖሊስ አገልግሎት አሰራሮች፣ ፖሊሲዎች፣ የአሰራር ስርዓቶችና ውጤቶች ጋር በተያያዘ ያወጣቸውን ሪፖርቶችና የሰበሰባቸውን መረጃዎች መከለስና መገምገም፤

3) የ APD ዓመታዊ በጀትና ወጪዎች መቀበል፣ መከለስና መገምገምና በጀት ነክ ምክረ ሃሳቦችን መስጠት፤

4) ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ቅጥርና ዓመታዊ ምዘናን በተመለከተ ለከተማው ምክር ቤት ምክር መስጠት፤

5) የቦርዱን ስራ በተመለከተ ይፋዊ ሪፖርቶች ማዘጋጀትና ሪፖርቶቹንም በሕትመት ኮፒና በኦንላይን ማሰራጨት፤ በዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች መሰረት በቀደመው የበጀት ዓመት ውስጥ ያከናወናቸውን ተግባራት በተመለከተ እስከ ሴፕቴምበር 1 ድረስ ለከተማው ምክር ቤት የጽሑፍ ሪፖርትና አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን አስተያየቶችና ምክረ ሃሳቦች ጨምሮ ያቀርባል፤

6) ቦርዱ ያከናወነው ግምገማና ምዘና ጋር የተያያዙ የሕግ፣ የፖሊሲ ለውጦችና ሌሎች እርምጃዎችን በምክረ ሃሳብነት ለከተማው ምክር ቤት፣ ለከተማው ስራ አስኪያጅ፣ ለ APD፣ ለት/ቤት ቦርድ፣ ለት/ቤት ዋና ተቆጣጣሪና ሌሎች መንግስታዊ ኤጄንሲዎች ማቅረብ፤

7) በአሌክሳንድሪያ ውስጥ ከፖሊስ አገልግሎት አሰራሮች፣ ፖሊሲዎችና የአሰራር ስርዓቶችና የቦርዱ ስራ ግምገማና ክለሳ ጋር የተያያዘ የማህበረሰብ አውትሪች ማካሄድ፤ እና

8) ቦርዱ በሕግ የተሰጠውን ዓላማ ለማሳካትና በከተማው በተሰጠው ፈቃድ መሰረት የፖሊስ ኤጀንሲዎችን በሚገባ ለመገምገም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።

ii. ቦርዱ የፖሊስ አሰራሮች፣ ፖሊሲዎችና የአሰራር ስርዓቶችን የተመለከቱ ምክረ ሃሳቦችን ለከተማው ምክር ቤት፣ ለከተማ ስራ አስኪያጅ እና ለ APD ሊያቀርብ ይችላል። ቦርዱ የደረሰባቸውን ግኝቶች፣ ምክረ ሃሳቦችና ደጋፊ ምክንያቶች በጽሑፍ በማዘጋጀት ምክረ ሃሳቡ ከጸደቀበት ቀነ ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለከተማው ምክር ቤት፣ ለከተማ ስራ አስኪያጅና ለ APD ማቅረብ አለበት።

a. የቦርዱ ምክረ ሃሳቦች ቦርዱ በሚያወጣቸው ይፋዊ ሪፖርቶች ውስጥ በሕትመት ቅጂና በኦንላይን ጭምር መካተት አለባቸው።

b. APD ከቦርዱ በተሰጠው ምክረ ሃሳብ መሰረት ማንኛውንም ለውጥ ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የፖሊስ አዛዡ የቦርዱ ምክረ ሃሳብ በደረሳቸው በ30 ቀናት ውስጥ የጽሑፍ መዝገብ በማደራጀት የቦርዱን ምክረ ሃሳብ ለመተግበር ፈቃደኛ ያልሆኑበትን ምክንያት ለከተማው ምክር ቤት፣ ለከተማ ስራ አስኪያጅና ለሕዝቡ ያሳውቃሉ።

**ክፍል 2-4-228 የፌዴራል፣ የግዛት ሕግና የከተማ ፖሊሲን ማክበር**

(a) ቦርዱ እያንዳንዱ አባል ተፈጻሚነት ያላቸውን የፌዴራል፣ የግዛትና የአካባቢ ሕጎችና የከተማ ፖሊሲዎች ማክበር አለባቸው።

(b) ቦርዱ የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ በሚያደርግበት ሁኔታና ከተማዋ ባጸደቀቻቸው አስተዳደራዊ ደንቦች መካከል ማንኛውም ግጭት ከተፈጠረ፣ በዚህ አንቀጽ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የከተማዋ አስተዳደራዊ ደንቦች የጸኑ ይሆናሉ። ወይም ይህን ክፍል ይሰርዙ የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት

(c) APD ለቦርዱ ያቀረባቸው ሁሉም ኦሪጂናል መዛግብት የ APD ኦፊሴላዊ መዛግብት በመሆናቸው እነርሱን ይፋ ማድረግ የሚቻለው አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት APD ከከተማዋ የአቃቤ ሕግ ቢሮ ጋር ምክክር አድርጎ ከወሰነ በኋላ ነው። ወይም ይህን ክፍል ይሰርዙ

**ክፍል 2-4-229 የማይካተቱ ጉዳዮች**

(a) ቦርዱ ከሚከተሉት ጋር የተያያዙ አቤቱታዎች ወይም ገዳዮችን አያስተናግድም፡

i. የከተማው ምክር ቤት የማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ቦርድን ለማቋቋም ከወሰነበት ከጁን 9/2020 በፊት የተፈጠረ ክስተትን የሚመለከቱ አቤቱታዎች ወይም 2019

ማስታወሻ: በቀይ የተሰጡ አስተያየቶች በምክር ቤቱ አባል በሰይፈልዴይን (Seifeldein) የቀረቡ ሲሆን በከተማው ምክር ቤትም ግምት ውስጥ ይገባል

(የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት)የከተማው ምክር ቤት የማህበረሰብ የፖሊሲ ግምገማ ቦርድ ለማቋቋም ከወሰነበት ቀን አንስቶ ነበር ፡፡

ii. ከስድስት ወር በፊት የተከሰተ ማንኛውንም ክስተት የሚያካትቱ አቤቱታዎችወይም ከ 6 ወርን ወደ ሲቪል ህጎች ውስንነት ደንብ ¨ብዙ ጊዜ 2 አመት ይለውጣሉ - ቅሬታውን ከማህበረሰቡ የፖሊስ ቁጥጥር ቦርድ ወይም ከ APD ጋር ከመታየት በፊት።

iii. የ APD የፋይናንስ አስተዳደር ወይም የግዥ ውሳኔዎች ወይም APD የወሰነው የቅጥር፣ የምደባና የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ ውሳኔዎች፤

iv. በአሁኑ ጊዜ ከጋራ ብልጽግና አቃቤ ሕግ ጋር በመሆን ምርመራ እየተካሄደባቸው ያሉ ጉዳዮች፣ በየትኛውም ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ የወንጀል ክስ፣ በሒደት ላይ ያለ ማንኛውም የወንጀል ክስ፣ በየትኛውም ፍርድ ቤት አሁን እየታዬ ያለ ወይም ለወደፊት ይከሰታል ተብሎ የሚጠበቅ የፍትሐ ብሔር ክስ (በክስ ማስታወቂያ ወይም በቀረበ አቤቱታ የሚረጋገጥ)የሚለው ይሰረዝ(የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት) ወይም በሰራተኞች የቅሬታ ማስተናገጃ ሒደቶች በኩል መፈታት ያለባቸውና ከከተማው አስተዳደር ሰራተኞች የሚቀርቡ ማናቸውም አቤቱታዎች ሌላኛው የምርመራ ሒደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ፤ እና የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት) ከ ወንጀል ምርመራ ከሚለው አስተያየት በላይ ያለውን ይመልከቱ እና

v. በዚህ አንቀጽ ወይም ተፈጻሚነት ባለው የግዛት ሕግ መሰረት ከቦርዱ የስልጣን ወሰን ውጭ ያለ ማንኛውም የመብት ጥያቄ።

ወይም 2-4-229 ይሰርዙ(የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት)

**ክፍል 2.4-230 የማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ደንብ ክለሳ**

(a) የከተማው ስራ አስኪያጅ ከቦርዱ፣ ከገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ፣ ከማህበረሰብ ባለድርሻዎች፣ ከ APD እና ከ APD ሰራተኞች ጋር በመመካከር ይህን ደንብና ውጤታማነቱን በተመለከተ ክለሳ በማካሄድ መሻሻል ያለባቸውን ምክረ ሃሳቦች ጨምሮ እስከ ኤፕሪል 1/2023 ድረስ ለከተማው ምክር ቤት ማቅረብ አለበት። ወይም አክል “ቦርዱ ስለ መሻሻል ምክረ ሀሳቦቹ ስለ ውጤታማነቱ የራሱን ተጨማሪ ሪፖርት ለካውንስሉ ያቀርባል” (የሰይልፈድን (Seifeldein) አስተያየት)

ክፍል 2. የአሌክሳንድሪያ ከተማ፣ ቨርጂኒያ፣ 1981 ሕግ ርዕስ 4 ምዕራፍ 1 አንቀጽ A (እንደተሻሻለው) በሚከተለው መልኩ ክፍል 4-1-5 እና 4-1-6 በማስገባት እንደዚህ ተሻሽሏል፡

**ክፍል 4-1-5 ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ**

የከተማው ምክር ቤት ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ የሚሾም ሲሆን የዚህ ሹመት ደንቦችና ሁኔታዎችም በቅጥር ውል ስምምነት ውስጥ ይገለጻሉ። ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ አገልግሎት የሚሰጠው የከተማው ምክር ቤት እስከፈለገው ድረስ ብቻ ነው። ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ከተማው አስተዳደር ቢሮ የሚመቻቸለት ሲሆን፣ ይህ ቢሮ ግን በአሌክሳንድሪያ ፖሊስ መምሪያ ሕንጻ ውስጥ መሆን የለበትም ወይም የከተማው አስተዳዳሪ ቢሮ የሚለውን ይጨምሩ (የሰይልፈድን አስተያየት)

ማስታወሻ: በቀይ የተሰጡ አስተያየቶች በምክር ቤቱ አባል በሰይፈልዴይን (Seifeldein) የቀረቡ ሲሆን በከተማው ምክር ቤትም ግምት ውስጥ ይገባል

**ክፍል 4-1-6 የገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ተግባራትና ኃላፊነቶች**

ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ፡

(a) ለማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት ገምጋሚ ቦርድ አስፈላጊውን አስተዳደራዊና የፖሊሲ ድጋፍ ይሰጣል፣ ቦርዱ ዓላማውን እንዲያሳካና የኃላፊነት ወሰኑን እንዲፈጽም ድጋፍ ያደርጋል፤

(b) በስራ ላይ ባሉት የከተማዋ የሰው ሐይል ስርዓቶችና የከተማ አስተዳደራዊ ደንቦች መሰረተ ገለልተኛ የፖሊስ ኦዲተር/መርማሪ ሰራተኞችን የመቅጠርና የመቆጣጠር፣ እንደዚሁም ከቅጥር ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን የመወሰን ስልጣን አለው፤

(c) የአሌክሳንድሪያ ፖሊስ መምሪያ ወቅታዊ ወይም ለወደፊት የታሰቡ የፖሊስ አሰራሮች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ የአሰራር ስርዓቶች፣ መመሪያዎችና ውጤቶች ላይ ገለልተኛ የሆነ ግምገማ በማካሄድ የግምገማውን ግኝቶችና ማንኛውም ተከታይ ምክረ ሃሳብን ለቦርዱ ያቀርባል፤

(d) ፖሊስ ለሕብረተሰቡ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች የሚያሻሽሉ ስርዓታዊ ለውጦችን የመለየት ዓላማ ያለው የጥራት ማረጋገጫ ስራን ያከናውናል፤

(e) የማህበረሰብ ቅሬታና የጉዳይ መከታተያ ስርዓት ይዘረጋል፣ ያስተዳድራል፤

(f) በከተማው ሕግ 2-4-227 መሰረት ለምርመራ ወደ ቦርዱ የተላኩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ክስተቶችን ይመረምራል፤

(g) የአሌክሳንድሪያ ፖሊስ መምሪያ የውጭ ጉዳይና ሙያዊ ሃላፊነት ቢሮ ያጠናቀቃቸውን ምርመራዎች ይገመግማል።

(h) APD በሚያካሂዳቸው የምርመራ ስራዎች ምክንያት የተወሰዱ ማናቸውንም የዲስፕሊን እርምጃዎች ይገመግማል፤ እንዲሁም

(i) ለቦርዱ ወይም ለመምሪያው በቀረቡ ቅሬታዎች ላይ የተጠናቀቁ ግምገማዎች ወይም ከመምሪያው የኃይል አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የተጠናቀቁ ግምገማዎች ጋር የሚገናኙ የአሌክሳንድሪያ ፖሊስ መምሪያ ሪፖርቶች፣ ፋይሎችና መዝገቦች እንደዚሁም የዲስፕሊን ነክ ሰነዶችን ጭምር ያለገደብ ማየት ይችላል።

(j) እንደዚህ ዓይነት የዲስፕሊን መዝገቦችንና የወንጀል ምርመራ ጉዳዮችን እነደዚሁም ቃሉን እንዲሰጥ በ APD በተጠየቀው መሰረት ቃሉን የሰጠ የ APD ፖሊስ መኮንን የሰጠውን ቃል ሚስጥራዊነት ማስጠበቅ አለበት። ይህን ዓይነቱን መረጃ ለቦርዱ ማጋራት ይችላል።

ክፍል 3. በዚህ ደንብ ክፍል 1 መሰረት የተሻሻለው ርዕስ 2፣ ምዕራፍ 4 እና በዚህ ደንብ ክፍል 2 መሰረት የተሻሻለው ርዕስ 4፣ ምዕራፍ 1 የአሌክሳንድሪያ ከተማ ሕግ አካል እንዲሆኑ ተወስኗል።

ክፍል 3. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ከጁላይ 1/2021 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

ጀስቲን ዊልሰን (JUSTIN WILSON)
ከንቲባ

መግቢያ፡

የመጀመሪያ ረቂቅ ማቅረብ፡

ረቂቅ 02192021 – ቅይጥ

ማስታወሻ: በቀይ የተሰጡ አስተያየቶች በምክር ቤቱ አባል በሰይፈልዴይን (Seifeldein) የቀረቡ ሲሆን በከተማው ምክር ቤትም ግምት ውስጥ ይገባል

1 ሕትመት፡
2 ሕዝባዊ ውይይት፡
3 ሁለተኛ ረቂቅ ማቅረብ፡
4 የመጨረሻ ማጽደቂያ